# በኢፌዲሪ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

## የ2014 በጀት ዓመት

## የመጀመሪያ ሩብ ዓመት

## የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ጥቅምት/2014 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# ማውጫ

መግቢያ ..... 3

1) የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት፡- (የትኩረት መስክ አንድ) ..... 4

2) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት (የትኩረት መሰክ አራት) ..... 12

3) የጥናትና ምርም አቅምን ማጎልበት ..... 15

4) ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ..... 16

አባሪ፡- የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም በትኩረት መስክ ..... 17

## መግቢያ

ዘርፉ ለሀገሪቱ እድገትና ልማት የሚያበረክተውን ወሳኝ አስተዋጽኦና ከሁሉም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር ያለውን ቁርኝት ከግምት ውስጥ በማስገባት ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አንዱ እንደመሆኑ መጠን በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ ከዘርፉ አንጻር የሚቀመጡ ዓላማዎችና ግቦችን መሠረት ያደረገ ስትራቴጂያዊና ዓመታዊ ዕቅዶች በየደረጃዉ በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ ሀገራችን እስከ አሁን ላስመዘገበችዉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የበኩሉን አዎንታዊ ሚና አበርክቷል::

በዚሁ መሰረት ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በ2014 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ የዘርፉን የውጤት ተኮር ዕቅድ ከባለድርሻ አካላት እና ከተጠሪ ተቋማት ጋር በጋራ በማቀድ፣በጋራ መድረክ ዕቅዱን በማዳበር ዕቅዱ በየደረጃው ባለው እርከን እንዲወርድ ተደርጓል፡፡

በዕቅዱ ላይ በተቀመጠው የድጋፍና ክትትል እና የግንኙነት አግባብ መሰረት የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

### በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በበጀት ዓመቱ የዝግጅት ምዕራፍ የዘርፉን የአስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ (2013-2022) መሠረት በማድረግ የ2013 በጀት ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ ተዘጋጅቷል፤
- ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከተጠሪ ተቋማት እና ከክልል ቢሮዎች የተውጣጡ ተሳታፊዎች በጋራ በ2013 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም እና የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ መግባባት ላይ በመድረስ እና ቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ ስምምነት በመፍጠር ውጤት ተኮር ዕቅዱ በየደረጃው እስከ ፈፃሚ እንዲወርድ ተደርጓል፡፡
- በተዘጋጀዉ የውጤት ተኮር ዕቅድ ላይ በየደረጃው በተደረሰው መግባባት አመራሩና ፈፃሚው የባለቤትነት ስሜት ይዞ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

1) **የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት፡-** (የትኩረት መስክ አንድ)

**ግብ 1. የአመራሩን እና የፈፃሚውን እውቀትና ክህሎት ማሳደግና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት**

- የስልጠና ፍላጎት በዳሰሳ ጥናት ተለይቷል፡፡
- ለ51 የክልል ባለድርሻ አካላትን እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያዎችን የስልጠና ፍላጎትና ክፍተትን መሰረት በማድረግ በኢንዱስትሪ ፓርክና ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት፣ ኦፕሬሽንና ማናጅመንት እና ፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ለ10 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፤
- በአግሮ ፕሮሰሲንግና ፋርማሲዩቲካልስ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ለሚገኙ 6 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በጨርቃጨርቅና አልባሳት ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እና ለተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ላይ ለተሰማሩ 132 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ210 (97 ወንድና 113 ሴት) ሰልጣኞች በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ክፍተትን መሠረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የጫማ ዲዛይን ክህሎት ለማዳበር በCAD/CAM ላይ ለ9 የኢንስቲትዩቱ የጫማ ተመራማሪዎች ለ3 ቀናት ተግባር ተኮር የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- 6 የኢንጂነሪንግ ተማሪዎች በሁለት ፋብሪካዎች ባቱ ቆዳና ኢትዮጵያ ቆዳ በመመደብ የተግባር ትምህርታቸውን እንዲካታተሉ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም 11 የጫማና የቆዳ ውጤቶች ተማሪዎች በአንበሳ ጫማ ፋብሪካ፣ በፎንተኒና ጫማ ፋብሪካ፣ በካንጋሮ ጫማ ፋብረካዎች  የተግባር ልምምድ አደርገዋል፡፡
- በብረታ ብረት ንዑስ ዘርፍ ለ4 የቴክኒክና ሙያ መምህራን የቲግ ወልድንግ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በንኡስ ዘርፉ በ2 (Machine Level 3, BMWuc, BMW level 1 እና GMFA level 3) የምዘና አይነቶች በአጠቃላይ ወንድ 27 ሴት 2 ድምር 29 የተመዘኑ ሲሆን  ወ-21 ሴት-2 በድምሩ 23 ባለሙያዎች የሙያ ደረጃ ምዘናውን ብቁ ሆነዋል፡፡
- በምግብ፣  መጠጥና  ፋርማሲዩቲካል  ለ63  ባለመያዎች  የአጫጭር  ጊዜ  ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ45 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ በሲዳማ ክልል በሳሙና ማምረት ዘርፍ ለተሰማሩ ወንድ 14 ሴት 3 በድምሩ 17 የኢንዱስትሪ ባለቤቶች የ10 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**የግብዓት አቅርቦት**

**ሰብዓዊ ግብዓት (የሰው ኃይል ማሟላት)**

**የሰው ኃይል**

- ለውሳኔ የሚረዳ የ769 ሠራተኞች መረጃ በፆታና በትምህርት ደረጃ ወቅታዊ ተደርጓል፡፡
- የሰው ሀይል ለለማሟት በተያዘው ዕቅድ መሠረት በክፍት የሥራ መደቦች ላይ ለውስጥ ሠራተኞች የደረጃ ዕድገት ማስታወቂያ በማውጣት ለ29 (ወንድ= 15 እና ሴት= 14) የውስጥ ሠራተኞች በደረጃ ዕድገት እንዲሟላ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለ2 ተላለኪ፣ ለ3 ጽዳት ሠራተኛ በድምሩ የአምስት ሴት ሠራተኞች ቅጥር ተከናውኗል፡፡

**ቁሳዊ ግብዓት**

- ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎችን ለማሟላት ጥረት ተደርጓል፡፡
- ለ104 የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- ለ103 ተሽከርካሪዎች 29,331 ሊትር ነዳጅ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም 36 ሊትር ቅባት ቀርቧል፤
- ለ1456 (95%) ተገልጋዮች የትራንስፖርት ስምሪት አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡
- ለ41 ተሽከርካሪዎች ጥገና ተደርጎሏል፡፡

**ግብ 2. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግ**

- ሁሉም የሥራ ክፍሎች የወረዳኔትና የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል::
- ዓለም አቀፍ፣ አትንጉራዊና ሀገራዊ የቨርቸዋል ስብሰባዎች እንዲካሄዱ ምቹ ሁኔታዎችን ተፈጥሯል፣
- እስከ ወረዳ ድረስ ባሉ የክልል ባለሙያዎች የጋራ የቴሌግራም ቻናል በማዘጋጀት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሲሰተም ላይ የሚገጥሙ ችግሮችን በመሰብሰብ እንደ አስፈላጊነቱ መፍትሄ እተሰጠባቸው ቆይቷል፣
- የሚኒስቴር መ/ቤታችን ሃላፊዎች የዋትስአፕ ቻናል እና የቴሌግራም ቻናል እንዲሁም የጋራ ኢሜል በመፍጠር ወቅታዊና ፈጣን መረጃዎች እንዲለዋወጡበት እና ውሳኔዎች የተሰጠባቸው ጉዳዮች በወቅቱ እንድተላለፉ ተደርጓል፤
- ኮቪድ-19ን ከመከላከል አንጻር በክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ በኢሜል እንዲያመክቱ በማድረግ አካላዊ ንክኪ ከግማሽ በላይ እንዲቀንስ ተደርጓል፤ በተጨማሪም ስብሰባዎች በኦንላይን ማካሄድ የሚያስችል ፕላት ፍርም በመግዛት ሚኒስቴር መ/ቤታችን፣ ክልሎችና ተጠሪ ተቋማት እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፣
- 18 ሲሲቲቪ ካሜራ እና የዲጂታል የፊረማ መቆጣጠሪያ በመግጠም አላስፈላጊ እንቅስቃዎችን ለመከታተል ተችሏል፣

**ግብ 3. ምቹ የሥራ አካባቢ በመፍጠር የፈፃሚዎችን ውጤታማነት ማሳደግ:-**

- ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎችን የማሟላት ስራ ተከናውኗል::
- የእርስ በርስ ግኑኝነት ዲሞክራሲያዊ በማድረግ የቡድን ስራ ስሜት በመፍጠር ለስራ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ተደርጓል::
- የህፃናት ማቆያ ማዕከል የሚያስፈልጉ ግብአት እና የሰው ኃይል በማሟላት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል::

**ግብ 4. የሙስና መከላከል ስርዓትን ማሳደግና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች አፈፃፀም**

- በተቋሙ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራርን በጋራ ለመከላከልና ሰራተኞች ጥቆማ የማቅረብ ባህላቸውን ለማሳደግ የተለያዩ የጥቆማ ማቅረቢያ መንገዶችን ማለትም ሳጥኖችን በየኮሊደሮች የማስቀመጥና በሳምንት ሁለት ጊዜ የመፈተሽ፤ የኢሜል አድራሻ ከፍቶ ለሰራተኞ የማስተዋወቅና በአካል ተገኝተው መጠቆም እንዲችሉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል::

- ከተቋሙ በዝውውር፣በጡረታ እና አገልግሎት ለሚያቋርጡ ሀብት አስመዝጋቢ ሰራተኞች የክሊራንስ አገልግሎት የመስጠት ስራ ተከናውኗል፡፡
- በኦዲት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወይም እንዲስተካከሉ ሪፖርት በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ ችግሮቹ መፈታታቸውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

- ከጥራት ሰርተፊኬት ማሻሻል፣ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ቅሬታ ጋር በተያያዘ ለቀረቡ 26 ቅሬታዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡
- በላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መዘግየትና በፍተሻ ውጤት ሪፖርት ላይ በደንበኞች የቀረበ ቅሬታን ለመፍታት ከኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በቅርበት በመነጋገርና ተቀናጅቶ በመስራት ችግሩን በተወሰነ መልኩ ለማሻሻል ጥረት ተደርጓል፡፡
- አዲስ በተሻሻለው የቆርቆሮ ደረጃ አተገባበር ላይ ከደንበኞች የቀረበ ቅሬታን ከኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ለመፍታት ተችሏል፡፡
- የንግድ ምዝገባና ፈቃድ መረጃ አሰጣጥችን በተሟላ መልኩ እንዲሰጥ ለማድረግ የባለሙያውን ግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ እና ስልጠና ተሰጥቷል፡፡መረጃዎቹ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲሰጥ አዳዲስ መረጃዎች በዌብሳይት በመጫን ሌሎችንም ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ለተገልጋዩ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- በአካል ለሚመጡ ተገልጋዬች መስፈርት በህጉ መስረት መሟላቱን በትክክል እንዲጣራ መስፈርቱም በጽሁፍ እንዲረጋገጥ እና ክትትል በማድረግ ተገልጋይ የተሟላ መረጃ ይዞ ለአገልግሎት እንዲገባ በማድረግ እየተሰራ ይገኛል፣
- ተገልጋዩ ቤቱ ሆኖ አገልግሎት መጠየቅ እና ማግኘት የሚያስችለውን ሲስተም በመፈተሽ በኦን ላይን የተጠየቁ አገልግሎቶችንም ሆነ ጥያቄዎች አስተያየቶች በመቀበል በአፋጣኝ መልስ እንዲሰጥ በማድረግ ለተገልጋዩ ፈጣን አገልግሎት ተሰጥቷል ፡፡

**ግብ 5. የዘርፉን ሥራዎች የሚያሳኩ የጥናት ስራዎችን ማካሄድ**

**የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ክለሳ በተመለከተ፤**

- የኢንዱስትሪ ፖሊሲን ለመከለስ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የፖሊሲ ክለሳ ጥናቱን 80% ደርሷል፡፡

**በልማት አጋሮች የሚደረጉ ድጋፎች በአንድ ማዕከል አሰባስቦ የመምራት**

- በተቀናጀ መልኩ ከዕቅድ ጋር በማስተሳሰር መምራትና መተግበር ይቻል ዘንድ የተዘጋጀው የልማት አጋር ድርጅቶች ድጋፍ አጠቃቀም እና አስተዳደር ሥርዓት ጥናት 55% ተከናውኗል፡፡

**ግብ 6. የሴቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ**

- ክትትልና ድጋፍ የሚደረግላቸዉን ኩባንያዎች ከሁሉም ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከተጠሪ ተቋማት የሴቶች ጉዳይ የስራ ክፍሎች ጋር በመተባበር 39 ኙን የመለየት ስራ ተሰርቷል፣
- በ2013 በጀት ዓመት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ አካቶ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑ ፋብሪካዎች/ ኩባንያዎች ለመደገፍ በታቀደው መሠረት በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባ መስተዳደር ከሚገኙ ፋብሪካዎች/ኩባንያዎች ለሠራተኞች በተለይም ለሴቶች ምቹ የስራ አካባቢን ከመፍጠርና ተሳታፊና ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ በተሰራው የዳሰሳ ጥናት በተገኘው ውጤት መሰረት በጨርቃጨርቅ ዘርፍ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች/ኩባንያዎች ከ UNIDO ጋር በመተባበር ለሁለት ቀን ለ28 ሴት ለ12 ወንድ በድምሩ ለ 40 ተሳታፊዎች በፆታ ጥቃት እና በሥርዓተ-ፆታ ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ የሁለት ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፤
- የሴቶችን የአመራርና የውሳኔ ሰጪነትን ሚና ለማጎልበት በGIZ ድጋፍ በተዘጋጀ የአቅም ማጎልበቻ አጭር ጊዜ የ3 ወር የገፅ ለገፅ ስልጠና ከተቋሙ 11 ከጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት 4 በድምሩ 15 በከፍተኛ ኤክስፐርት፣ በቡድን መሪና በዳይሬክተር ደረጃ የሚገኙ ሴቶች አጠናቀው ተመርቀዋል፡፡ ሂደቱን ክትትል የማድረግና የመገደፍ ስራ ተሰርቷል፡፡
- በ2013 በጀት ዓመት ሴቶች በአመራርና ውሳኔ ሰጪነት የሥራ መደቦች በዳይሬክተር ደረጃ ከነበረው 11 ነባራዊ መነሻ ወደ 12 እንዲሁም በቡድን መሪ ደረጃ ከነበረው 25 ነባራዊ መነሻ ወደ 26 ከፍ ብሏል፡፡

**ግብ 7. የኮሚኒኬሽን ሥራን በቀጣይነት ተደራሽ በማድረግ የዘርፉ ገጽታ መገንባት**

- 3 የፕረስ መግለጫዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 5 የፕረስ መግለጫዎች ተዘጋጅተው በሚዲያዎች ተደራሽ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ 167 በመቶ ነው፡፡

- 75 ዜና ለማዘጋጀት ታቅዶ 168 ዜና ተዘጋጅቶ በተለያዩ ሚዲያዎች ሽፋን እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ 224 በመቶ ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከፍ ያለበት ምክንያት በወቅታዊ ጉዳይ በሆነው በኑሮ ውድነት ላይ ተከታታይ ዜናዎች በመሰራታቸው ነው፡፡
- በበጀት ዓመቱ ባለፉት ሶስት ወራት 1 ፕረስ ኮንፍረንስ በማዘጋጀት መረጃዎችን ለተለያዩ ሚዲያዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 5 ተከናውኗል፡፡
- ባለፉት ሶስት ወራት 3 አርቲክሎች ለመስራት ታቅዶ 8 የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙም 267 በመቶ ነው፡፡
- በተለያዩ ጉዳዮች በአወንታ 60 እንዲሁም 25 በሚዛናዊነት በድምሩ 85 ዘገባዎች ሞኒተሪ የተደረጉ ሲሆን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ በተሳሳተ መረጃ በአሉታዊ የተዘገበ ዘገባ የለም፤
- የመስሪያ ቤቱን ልዩ ልዩ የስራ እንቅስቃሴዎችን አስመልክቶ በቃል፣ በጹሁፍና በስልክ በመረጃ ፈላጊዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ከተገልጋዮችና ደንበኞች ለሚቀርቡ የቃል፣ የስልክ፣ የጽሑፍ መረጃ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት 447 ታቅዶ 410 ማከናወን ተችሏል፡፡
- **ሁነት መፍጠርና መምራት፡-** ስለ ኑሮ ውድነት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ፣ ለመከለከያ ሰራዊት ድጋፍ የሚደረግበት መድረክ፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስ አዲስ አበባ ኮንሶ፣ የችግኝ ተከላ አዲስ አበባና ኮንሶ፣ የ2013 በጀት ዓመት አፈጻጸም እና 2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ውይይት (ከተቋሙ ሰራተኞች፣ ከተጠሪ ተቋማት፣ ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ አመራሮች ጋር)፣ በ2013 በጀት ዓመት የተሻለ አፈጻጸም ያሳዩ ላኪ ኩባንያዎች እውቅና ፕሮግራም፣ የተቋሙ ሰራተኞች የሚበረታቱበትና እውቅና የሚሰጡበት ብሎም ለረጅም ዓመታት ያገለገሉ የተቋሙ ሰራተኞች የሚታወሱበትና የሚሸለሙበት መድረክ፣ "የነጩ ፖስታ ጎርፍ ወደ ነጩ ቤተ መንግስት" በተቋሙ ሰራተኞች እንዲሁም ከተቋሙ 16 ተጠሪ ተቀዋማት ጋር ተዘጋጁ መድረኮችን የማዘጋጀት እና የማስተባበር ስራ ተሰርቷል፡፡

**ግብ 8፡-ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር**

- የቆዳ ፋብሪካዎች እያጋጠማቸዉ ያለዉን የደረቅ ቆሻሻ ማወገጃ ቦታ ችግር እና ሌሎችንም ተያያዥ ችግሮች ከባለድርሻ አካላት ጋር የአካባቢ፤ደንና አየር ንብረት ለዉጥ ኮሚሽን፤ ከአ.አ.፤ ከአማራ፤ ከኦሮሚያና ሞጆ አካባቢ ጥበቃ፤ከአ.አ.ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እንዲሁም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተቀናጅቶ በመስራት፣ስራዎችን

በመከታተልና በመገምገም፤ የሚከሰቱ ችግሮችን በጋራ ተወያይቶ መፍትሄ እንዲያገኙ እየተሰራ ነው፡፡

- ዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪ ትስስር፡- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የ2ኛና 3ኛ ዓመት የቴክስታይልና የጋርመንት ተማሪዎች በኢንስቲትዩቱ በምርምርና ፍተሻ ዳይሬክቶሬት፤ ይርጋለም ጨ/ፋብሪካና በMNS ጨ/ፋብሪካ በእያንዳንዱ የአንድ ቀን ስልጠና እንዲያገኙ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ 2 የ5ኛ ዓመት የጨርቃጨርቅ ኢንጂነሪንግ ተማሪዎች በምርምርና ፍተሻ ዳይሬክቶሬት የመመረቂያ የምርምር ስራቸውን እንዲሰሩ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡
- ለኢትዮ ኢንጅነሪግ ግሩፕ ለምርቶቻቸው የምርት ጥራት ደረጃ ለማዘጋጀት መድረክ ተፈጥሮ ከስምምነት ተደርሷል፡፡ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንስ ጋር በዓመታው የደረጃዎች ዝግጅት ምክክር ተደርጓል፡፡
- በምግብና መጠጥ ንዑስ ዘርፍ የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስተሪ ትስስር መነሻ እቅድ ለ17 ዩኒቨርሲቲዎች ተልኮ 10 ዩኒቨርሲቲዎች እቅድ አዘጋጅተው እንዲልኩ ተደርጓል፡፡
- በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት እንዲሁም ከከተማ መስተዳድር እና ከተለያዩ ሚኒስቴር መስርያ ቤቶች ጋር በእቅድ በተያዘው መሰረት በኢንዱስትሪዎች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ቅንጅታዊ መድረኮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡
- በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላትና ሌሎች ተዋንያን በጋር ለመስራት ስምምነት ላይ ተደሷል፡፡
- ከፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ እና ከባለድርሻ አካላት በጋራ ተባብሮ ለመስራት የሚያስችል ውይይት ተደርጓል፡፡

## 9. መረጃ በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን፣ ተደራሽነት ማሳደግ

- ከውስጥ የስራ ክፍሎች ፣ከክልልና ከከተማ አስተዳደሮች፣ ከባለድርሻ አካላትና ከተጠሪ ተቋማት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የዕቅዱን 100% ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡
- ለውስጥና ለውጪ መረጃ ተጠቃሚዎች በተለያዩ የንግድ ዘርፎች የተሰጡ መረጃዎች በዚህ ሩብ ዓመት ዕቅድ 150 ለመስጠት ታቅዶ 154 ተሰጥቷል ፣ አፈጻጸም 103%፡፡
- የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ስታቲስቲክስ ዝግጅት ግብዓት የሚሆን የንግድ፣ ኢንዱስትሪና የገበያ መረጃ አይነቶችና ምንጮች ለመለየት ተችሏል፡፡

- የተለዩትን የንግድ፣ኢንዱስትሪና የገበያ መረጃ አይነቶችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች (ተቋማት) መረጃ የመሰብሰብና የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡
- ከተለያዩ የግብይት ማዕከላት በተዘረጋው ሀገራዊ የገበያ መረጃ ሲስተም መሰረት ከአምስት ክልሎች የአምስት የግብርና ምርቶች በሶስት ቋንቋዎች መረጃ ከ157 ወረዳ የግብይት ቦታዎች በነጻ የድምጽ መልዕክት በ6077 የገበያ መረጃ እተሰበሰበ እየተሰራጨ ይገኛል፡፡

**2) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት (የትኩረት መስክ አራት)**
**ግብ 1:- የማምረት አቅም አጠቃቀም ማሳደግ**

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል የተያዙ ግቦችን ለማሳካት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ለጨርቃጨርቃና ቆዳ አምራች ኢንዱስትሪዎች የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እንዲያገኙ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በዚህም ዋሊያ ቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ዴኤስ ኤፍ ኬሚካልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ኤልቴክስ ቴክስታይል ኤንድ ጋርመንት ፋክትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ሁዋክሱ ቴክስታይል ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ አርባምንጭ ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማህበር በድምሩ 2,086,000.00 የአሜሪካ ዶላር እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- 4 የቆዳና ቆዳ አምራች ኢንዱስትዎች( ካባና፣ ፒኤስ ቬንቸር፣ ኮት ኬትና ብዒተ በረባሶ) ምርታቸውን ኤክስፖርት ለማድረግ አየር መንገዱ የቦታ ጥበት ምክንያት ምርታቸውን ለመላክ ችግር የገጠማቸው መሆኑን ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ ባቀረቡት የድጋፍ ጥያቄ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ከፍተኛ ኃላፊዎች ጋር በመወያየት ችግሩ የበላይ አመራር አቅም በመጠቀም እንዲፈታ ተደርጎ ምርታቸውን ኤክስፖርት አድርገዋል ፡፡
- የጨርቃጨርቅና ጋርመንት አለም አቀፍ ዋና ዋና ገዥ ከሆኑት እና በአገራችን ከሚገኙ ትላልቅ አምራች ኢንዱስትዎችን ያካተተ የ"buyer forum" በዋና ዋና አጀንዳዎች በተለይም ከሎጀስቲክስ፣ AGOA፣ Ease of doing business እንዲሁም አጠቃላይ የመንግስት አቅጣጫዎች ላይ ያላቸውን ጥያቄ አንስተው ምላሽ የተሰጠበትና በስራው ላይ አመኔታ እንዲጨምሩ አግዟል፡፡
- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የኤክስፖርት ስራ ለማድረግ በ2014 ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚሰሩ ስራዎች የትስስር ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- የቆዳ ውጤት አምራች ባለቀለት የቆዳ ቦርሳ ምርት ላይ ከውጭ ደንበኞች በስም የተዘጋጀ ቦርሳ እንዲቀርብላቸው በጠየቁት መሰረት ግብዓቱን ማግኘት እንዲችሉ ከማር ሰም አምራች ድርጅቶች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ተደርጓል፡፡
- በማምረት ላይ ላሉ ለ 14 በአግሮ ፕሮሰሲንግ የተሰማሩ ፋብሪካዎች ድጋፍና ክትትል በማድረግ፣ በማምረት ሂደት ላይ ያሉ ችግሮችና ያስከተሉት ጉዳት ተለይተዋል፤መፍትሄ የሚሆን ምክረ ሃሳብም ቀርቧል ፡፡

**ግብ 2. የወጪ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ**

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሦስት ወራት ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ 125.573 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቀዶ 117.843 ሚሊዮን ዶላር (93.8%) ማሳካት ተችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም ከአምናው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወራት ከተገኘው 95.24 ሚሊዮን ዶላር ጋር ሲነፃፀር በ22.6 ሚሊዮ ዶላር (23.7%) ብልጫ አስመዝግቧል፡፡

**ግብ 3. የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ማሳደግ**

ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው ንዑስ ዘርፎች የግብዓት አቅርቦት ለማሟላት የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የፓልም ዘይት አምራች ድርጅቶች የፓልም ድፍድፍ ዘይት ገዝተው ሲያስገቡ ይከፍሉት የነበረው 11% ባንክ ቻርጅ እንዲነሳ በደብዳቤ በተጠየቀው መሰረት ወደ 5.5% ዝቅ እንዲል ተደርጓል ፡፡
- የፓልም ድፍድፍ ዘይትን በግብአትነት ተጠቅመው ዘይት ለሚያጣሩ 3 ፋብሪካዎች 35,742 ቶን ድፍድፍ ዘይት በማቅረብ 26,806 ቶን ዘይት ተጣርቶ ለህዝብ ቀርቧል ፡፡
- የምግብ ዘይት አምራች ፋብሪካዎችን የግብአት እጥረት ችግርን ለመፍታት ሙሉ ማጣሪያ ላላቸው ፋብሪካዎች ከውጭ ሃገር ድፍድፍ ዘይትና ጥሬ ግብአት አስገብተው በሃገር ውስጥ አቀናብረው ለገበያ በማቅረብ አሁን ያለውን የምግብ ዘይት የአቅርቦት ክፍተት መሙላት እንዲችሉ ለ 30 ፋብሪካዎች የግብአትና፣ የውጭ ምንዛሬ ፍላጎት በመለየት ለውሳኔ የሚረዳ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ ቀርቧል ፡፡
- አኩሪአተርን በግብአትነት የሚጠቀሙ 20 ፋብሪካዎች መረጃ ተደራጅቷል፡፡
- ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ በቁጥር 5 ሚሊየን ጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅርቦት በማመቻቸት ከአዲስ አበባ አቅራቢዎች 878,917 (የበሬ 80,618፣ የበግ 448,412፣የፍየል 349,887)፣ ከአማራ ክልል 144,290 (የበሬ 3,550፣የበግ 114,406፣የፍየል 26,334) ፣ ከኦሮሚያ ክልል 707,939 (የበሬ 123,507፣የበግ 258,628፣ የፍየል 326,104) ፣ ከደቡብ ክልል 272,190 (የበሬ 92,282፣የበግ 125,300፣ የፍየል 54,608) ፣ በድምሩ 2,003,336 (የዕቅዱ 40%) ጥሬ ቆዳና ሌጦ ተሰብስቦ የማስተሳሰር ስራ ተሰርቷል ፡፡ እንዲሁም 7.5 ሚሊዮን ኪ.ግ. የቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ኬሚካል ለማቅረብ ታቅዶ 2.5 ሚሊዮን ኪ.ግ. ኬሚካል (ከዕቅዱ 33 በመቶ) ለፋብሪካዎች ቀርቧል፡፡

**ግብ 4. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ድርጅቶች የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶችን ተጠቅመው በአለምና በሀገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማበረታታት**

- 12 የጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ምርቶች ላይ ለሚነሱ የስታንዳርድ የግብአት ምርት ጥምርታ ጥያቄዎች ማስተካከያዎች ለማድረግ ታቅዶ አፈፃፀሙ 14 ሆኗል፡፡
- 6 ድርጅቶች አዲስ የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚነት ሠርተፊኬት ለመስጠት ስርዓቱን ለመጠቀም ጥያቄ ያቀረቡ ድርጅቶች 10 በመሆናቸው ምክንያት ክንውኑ የዕቅዱ 167% ሆኗል፡፡
- የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ ያቀረቡ 2 ድርጅቶች የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት ጥያቄያቸው ምላሽ አግኝቷል፡፡
- ለ21 (91%) የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚነት እድሳት የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት የሰርተፍኬቶች እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡
- የግብዓትና ምርት አቅርቦት ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ 23 (76.7%) ድርጅቶች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ውል የተፈራረሙ ሲሆን ውሎቹን እና በተዋዋዮቹ የቀረቡትን የግብዓት ምርት ጥመርታዎች በማፅደቀ ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች እና አገልግሎት ሰጪዎች የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡
- ለ19 (111.7%) የተለያዩ ማስተካከያ (የተጨማሪ ግብዓት፣ የመለኪያ ለውጥ ማስተካከያ፣ የተተካኪ ግብዓት፣ የግብዓት ጥምርታ ለውጥ) ጥያቄዎችን በመመርመር የግብዓት ምርት ጥመርታው እንዲፀድቅላቸው ተደርጓል፡፡
- ለ8 የጉምሩክ ሁለተኛ ምድብ ሀ ታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚነት ጥያቄ ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ግብዓት ምርት ጥመርታ በማዘጋጀት ሠርተፊኬት ታድሷል፡፡ እንዲሁም ለ7 አዲስ የሁለተኛ ታሪፍ ምድብ ሀ ማበረታቻ ተጠቃሚዎች ጥያቄ ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ግብዓት ምርት ጥመርታ በማዘጋጀት ሰርቲፍኬት ተሰጥቷል፡፡
- ለ1 ድርጅት የግብዓት መጠቀሚያ/ መሽጫ ጊዜ እንዲራዘምለት ተደርጓል፡፡

**ግብ 5. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ**

5.1 በግንባታ ሂደት የነበሩ እና ወደ ማምረት የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች በየንዑስ ዘርፉ፡

- ብረታብረት 2 ታቅዶ አፈፃፀም 2 (100%)፤
- ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል 8 ታቅዶ አፈፃፀም 9 (112%)፤

### 5.2 አዳዲስ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ማበራከትና ነባሮችን ማጠናከር

- 435 አዳዲስ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ አፈፃፀሙ 311 (71.5%) ሆኗል፡፡
- 3,939 አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን የማጠናከር ስራ ተከናውኗል፡፡
- በ18 SME የኢንዱስትሪ ክላስተር በነባርና በአዲስ ቦታዎች ላይ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ11 (61%) ተደርጓል፡፡
- ለክልሎች/ፓርኮች/ክላስተሮች/RTCs ከመስክ መልስ በእቅድ እና በአፈጻጸም ላይ 3 (100%) ጊዜ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡
- የቡልቡላ ፓርክና መቂ የገጠር የሽግግር ማዕከላት የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታ አፈጻጸም 70% ደርሷል፡፡

### ግብ 6. የአረንጓዴ ማኑፋክቸሪንግ ስትራቴጂና ኢነርጂ ኢፊሸንሲ ስትራቴጂ በመተግበር የካርበን ልቀትን መቀነስ

- የፋብሪካዎችን የኃይል አጠቃቀም መጠን እና አይነት ደረጃ (baseline) ጥናት ለማካሄድ ቢጋር ተዘጅቷል፡፡
- የአረንጓዴ አሻራ <<ኢትዮጵያን እናልብሳት>> በሚል መርሃ ግብር በ 3 ዙር 12,000 የተለያዩ ችግኞች በቦሌ ለሚና በቅሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተከላ ተከናውኗል፡፡
- የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት /MRV ስርአትመዘርጋት የሚያስችል መግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ከ6 ተጠሪ ተቋማት ለመፈራረም በሂደት ላይ ነው፡፡

### ግብ 7. ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል ማሳደግ፣

በኢንዱስትሪ አዳዲስና ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ሂደታቸውን በማፋጠን ለ41.9 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ኢንስቲትዩቶች በሚከታተሏቸው እና ወደ ማምረት በተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች ለ19.4 ሺህ (46%) ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

### 3) የጥናትና ምርምር አቅምን ማጎልበት

በሩብ ዓመቱ ችግር ፈቺ ጥናቶች አፈፃፀም በየንዑስ ዘርፍ ሲታይ፦

- ጨርቃጨርቅ 2 ታቅዶ አፈፃፀም ጥናቶች ተጀምሯል ፤
- ቆዳና የቆዳ ውጤቶች የጫማ ፋብሪካዎች ምርታማነትንና ተወዳዳሪነታቸውን የሚያግዙ አዳዲስ ምርቶች በመስራት የምርት ስብጥራቸውን እንዲያስፋፉ ከማድረግ አኳያ አዳዲስ የጫማ ሞዴሎች ለመስራት የሚረዱ የፓተርን ግሬዲንግ፤የዲዛይን (መዝገብ ብዜት በቁጥር እና ፍጆታ ልኬት) ለአራት ጫማ አምራች ኩባንያዎች (ኤሊኮ/ለጥቁር አባይ፤ ሞደርን ዘጌ ፤ካንጋሮ፣ እና ራምሴ ጫማ) በድምሩ 33 ሴሪ የፓተርን ግሬዲንግ ስራ ድጋፍ ተድርጓል፡፡ አፈፃፀሙ ከዕቅዱ አንፃር ሲታይ 66 በመቶ ነው ፡፡
- ብረታብረት 13 ታቅዶ አፈፃፀም 10 የተጀመሩ ጥናቶች፤
- ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል 4 ታቅዶ አፈፃፀም 2 (50%)፤
- ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች 3 ታቅዶ አፈፃፀም 2 (67%)፤

## 4) ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- የውጪ ምንዛሬ እና የስራ ማስኬጃ ፋይናንስ አቅርቦት፤
- የግብዓት አቅርቦት፤
- የመሰረተ ልማት (የመስሪያ ቦታ፣ የሃይል፣ መንገድ) አቅርቦት መሟላት፤
- የቅንጅት ስራዎች፤
- የኢንደስትሪ ሰላም፤
- በቆዳው ንዑስ ዘርፍ ከፍተኛ የኤክስፖርት ድርሻ ያለው ሁዋጂያን ኢንተርናሽናል ላይት ኢንዱስትሪ ሲቲ (ኢትዮጵያ) ከመጋቢት 2013 ጀምሮ የምርት ሥራ ማቆም፣
- በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ያሉ የጫማ ክላስተር ባለሀብቶች የተሰጣቸውን ቦታ ውጤታማ በሆነ መልኩ አለመጠቀም፤ እንዲሁም በክላስተር ውስጥ 8 ሺህ ካሬ ሜትር የተለየ ክፍት ቦታዎች ለአልሚዎች አለመተላለፍ፣
- የሞጆ ሌዘር ሲቲ ኢንዱስትሪ ፓርክ ፕሮጀክት ወደ ተግባር ለማስገባት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በማጠናቀቅ በፍጥነት ወደ ተግባር ሥራ መግባት ትኩረት የሚፈልግ መሆኑ፤
- በሞጆ አካባቢ ያሉ የቆዳ ፋብሪካዎች የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የተከለከለ በመሆኑና አማራጭ ቦታ ባለመዘጋጀቱ በድርጅታቸው ውስጥ የተከማቸ መሆኑ፣

## አባሪ፡- የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም በትኩረት መስክ

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የመጀመሪያ ሩብ ዓመት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| **ሀ** | **የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት (ትኩረት መስክ አንድ)** | | | | | |
| 1 | የአመራሩንና የፈፃሚዎችን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ማሻሻል | | | | | |
| 1.1 | በሚኒስቴር መ/ቤቱ (የተሰጠ የአቅም ግንባታ ስልጠና)፣ | በቁጥር | 82 | 67 | 81.7 | |
| 1.2 | የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 132 | 210 | 159 | ለ210 (97 ወንድና 113 ሴት) ሰልጣኞች በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች (የመሰረታዊ ልብስ ስፌት፣በኮመፒውተር የታገዘ የጥልፍ ስራ፣ ኮምፒተራይዝድ ፓተርን ሜኪንግ ….) ክፍተትን መሠረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ |
| | | በቁጥር | | 12 | | የኦዲት አሰራር ስርዓት (Auditing Management System ISO 19011:2018) ላይ 12 ባለሙያዎች በኢትዮጵያ አክሪድቴሽን ጽ/ቤት አሰልጣኝነት ስልጠና ተከታትለዋል፡፡ |
| 1.3 | የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | | 9 | | የጫማ ዲዛይን ክህሎት ለማዳበር በCAD/CAM ላይ ለ9 የኢንስቲትዩቱ የጫማ ተመራማሪዎች ለ3 ቀናት ተግባር ተኮር የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ |
| | | በቁጥር | | 17 | | ▪ 6 የኢንጂነሪንግ ተማሪዎች በሁለት ፋብሪካዎች ቆዳ ፋብሪካዎች በመመደብ የተግባር ትምህርታቸውን እንዲካታተሉ የተደረገ ሲሆን፣<br>▪ 11 የጫማና የቆዳ ውጤቶች ተማሪዎች በሦስት የጫማ ፋብረካዎች የተግባር ልምምድ አደርገዋል፡፡ |
| | | በቁጥር | | 16 | | የኢንስቲትዩቱ 6 ባለሙያዎች እንዲሁም የቆዳ እቃዎች አመራረት ከ16 ተመዛኞች ውስጥ 10 ሰልጣኞችን በደረጃ ሁለት የሙያ ብቃት ምዘናን ተመዝነዉ ብቁ ሆነዋል፡፡ |
| 1.4 | የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት /ለንዑስ ዘርፉ ባለሙያዎች የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና መስጠት/ | የሰለጠኑ ሠልጣኞች ብዛት በቁጥር | 25 | 4 | 16 | |
| | | የተመዘኑ ባለሙያዎች በቁጥር | 25 | 29 | 116 | ለ4 የቴክኒክና ሙያ መምህራን የቲግ ወልድንግ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በንኡስ ዘርፉ በ2 (Machine Level 3, BMWuc, BMW level 1 እና GMFA level 3) የምዘና አይነቶች በአጠቃላይ 29 የተመዘኑ ሲሆን 23 ባለሙያዎች የሙያ ደረጃ ምዘናውን ብቁ ሆነዋል፡፡ |
| | በዩኒቨርሲቲ ኢንደስትሪ/ | በቁጥር | 40 | 22 | 55 | በብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቱዩት ከተለያዩ 4 |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የመጀመሪያ ሩብ ዓመት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | ቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋማት ቅንጅታዊ የትስስር ፎረም በኢንተርን ሺፕ የሰው ኃይል አቅም መገንባት | | | | | ዩኒቨርሲቲዎች ለመጡ 16 ተማሪዎች ስልጠና አያገኙ ሲሆን የሱ በተባለ የግል ድርጅት 6 ተማሪዎች የኢንተርን ሺፕ ስልጠና እንዲያገኙ ተመድበዋል፤ |
| 1.5 | የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 63 | 45 | 71 | ለ45 የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ተሰጥቷል፤ |
| 1.6 | የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 17 | 17 | 100 | በሲዳማ ክልል በሳሙና ማምረት ዘርፍ ለተሰማሩ 17 የኢንዱስትሪ ባለቤቶች የ10 ቀናት ስልጠና ተሰዋቷል፡፡ |
| 1.7 | የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ባለስልጣን /ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ህብረተሰብ ክፍሎች/ | በቁጥር | 1728 | 1269 | 73 | |
| | በአካባቢ ጥበቃና ኢነርጂ አጠቃቀም ላይ ግንዛቤ የተፈጠረላቸው የኢንዱስትሪ ባለሃብቶችና ሠራተኞች | በቁጥር | 2717 | 82 | 3 | |
| **ለ** | **የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት (ትኩረት መስክ ሁለት)** | | | | | |
| 1 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም አጠቃቀም ማሳደግ | | | | | |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | በመቶኛ | 70 | 52 | 74 | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | በመቶኛ | 53 | 35.9 | 68 | |
| | ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | በመቶኛ | 10 | 15.9 | 100 | በሩብ ዓመቱ በመሰረታዊ ብረታ ብረት 8.1 በመቶ፣ በኢንጅነሪንግ ምርቶች 27.395 በመቶ፣ እና በኤሌክትካልና ኤሌክትሮኒክስ 12.26 በመቶ በአማካይ 15.92 በመቶ አቅም ማምረት ተችሏል፡፡ |
| 2 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች የኤክስፖርት ገቢ ማሳደግ | | | | | |
| | ጨርቃጨርቅና አልባሳት ን.ዘርፍ | በሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር | 45,783.36 | 44,050.80 | 96.2 | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የመጀመሪያ ሩብ ዓመት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | ቆዳ ኢንዱስትሪ ን.ዘርፍ | ›› | 14,532.37 | 10,616.70 | 73 | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | ›› | 24,941.36 | 25,729.56 | 103 | |
| | ሥጋና ወተት ን.ዘርፍ | ›› | 25,650 | 27,490.91 | 107 | |
| | ብረታብረትና ኤሌክትሮኒክስ | ›› | 11,611.50 | 4,976.59 | 43 | |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች | ›› | 3,055.10 | 4,978.82 | 163 | |
| | **ድምር** | በሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር | **125,573.59** | **117,843.38** | **93..8** | |
| 3 | በተመረጡ ስትራተጂክ ተኪ ምርቶች የአገር ውስጥ ምርት ድርሻ ማሳደግ | | | | | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | በመቶኛ | 29.1 | 42.5 | 146 | • የምግብ ዘይት፣ ፓስታና አልሚ ምግቦች፣ብቅል እና መድሀኒት በሀገር ውስጥ የተመረተ 307,208 ቶን ሲሆን ከዉጭ የገባ 415,889.70 ቶን ነው። |
| 4 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የግብዓት አቅርቦት ማሳደግ | | | | | |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | በቶን | 1,710,323 | 861,215 | 50.4 | • 547,578 ቶን ከሀገር ውስጥ የቀረበ ግብዓት ነው። |
| | የቆዳ ኢንዱስትሪ | በቁጥር | 5,000,000 | 2,003,336 | 40 | በቁጥር 5 ሚሊየን ጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅርቦት በማመቻቸት ከአዲስ አበባ አቅራቢዎች 878,917 (የበሬ 80,618፣ የበግ 448,412፣የፍየል 349,887)፣ ከአማራ ክልል 144,290 (የበሬ 3,550፣የበግ 114,406፣የፍየል 26,334)፣ ከኦሮሚያ ክልል 707,939 (የበሬ 123,507፣የበግ 258,628፣ የፍየል 326,104)፣ ከደቡብ ክልል 272,190 (የበሬ 92,282፣የበግ 125,300፣ የፍየል 54,608)፣ በድምሩ 2,003,336 (የዕቅዱ 40%) ጥሬ ቆዳና ሌጦ ተሰብስቦ የማስተሳሰር ስራ ተሰርቷል ። |
| | | በሚሊዮን ኪ.ግ. | 7.5 | 2.5 | 33 | ባለፉት ሶስት ወራት 7.5 ሚሊዮን ኪ.ግ. የቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ኬሚካል ለማቅረብ ታቅዶ 2.5ሚሊዮን ኪ.ግ. ኬሚካል (ከዕቅዱ 33 በመቶ) ለፋብሪካዎች |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የመጀመሪያ ሩብ ዓመት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | | በኩንታል | 1950 | 1550 | 79.5 | ከደርባን ሲሚንቶ ፋብሪካ ለቆዳ ፋብሪካዎች ለማቅረብ ዕቅድ ተይዞ 1550 ኩንታል (79.5 በመቶ) ኖራ ለ8 ቆዳ ፋብሪካዎች እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች (የሀገር ውስጥ ግብዓት ድርሻ) | በመቶኛ | 90 | 73 | 81 | • የገበያ ትስስር በመፍጠር አምራች ኢንዱስትሪው የሀገር ውስጥ ግብአትን ለመጠቀም የሚያስችል ስራ ተሰርቷል፡፡ |
| 5 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ | | | | | |
| | በግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ ድጋፍና ክትትል ማድረግ | ወደ ማምረት የተሸጋገሩ ፕሮጀክቶች በቁጥር | 10 | 11 | 100 | ብረታ ብረት 2፣ ምግብ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል 9 በድምሩ 11 ፕሮጀክቶች ወደ ማምረት ተሸጋግረዋል፤ |
| | የተቋቋሙ አዳዲስ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች | በቁጥር | 435 | 312 | 71.7 | |
| | በSME የኢንዱስትሪ ክላስተር በነባርና በአዲስ ቦታዎች ላይ ድጋፍና ክትትል የተደረገላቸው የኢንዱስትሪ ባለቤቶች ብዛት | በቁጥር | 18 | 11 | 61 | በክላስተር ድጋፍ በተመለከተ ከGIZ ባለሙያ ጋር በመሆን በአማራ እና በሲዳማ ክልሎች በምግብ ማቀነባበር፣በወተት ማቀነባበር፣ሙዝ ፕሮሰሲን፣የእንስሳት መኖ ማቀነባበር ላይ በተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ላይ የመስክ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ |
| | በክልሎች/ፓርኮች/ክላስተሮች/RTCs ከመስክ መልስ በእቅድ እና በፈጻጸም ግምገማ የተሰጠ ግብረ መልስ | በቁጥር | 3 | 3 | 100 | |
| 6 | በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ድርጅቶች የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶችን ተጠቅመው በአለምና በሀገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማበረታታት | | | | | |
| | ስታንዳርድ የግብአት ምርት ጥምርታ በተዘጋጀላቸው የጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ምርቶች ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን በማጣራት ማስተካከያዎች ማድረግ | በቁጥር | 12 | 14 | 116.7 | |
| | አዲስ የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚነት ጥያቄ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ | በቁጥር | 6 | 10 | 167 | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የመጀመሪያ ሩብ ዓመት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት ሰርተፍኬት መስጠት | | | | | |
| | የቀረጥ ተመላሽ ተጠቃሚነት ጥያቄ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት ማስተናገድ | በቁጥር | 2 | 2 | 100 | |
| | የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚነት እድሳት ጥያቄ ሲቀርብ የጥያቄያቸውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ስ/ግ/ም/ጥመርታ ላልወጣላቸው ዘርፎች ግ/ም/ጥመርታ በማዘጋጀት የሰርተፍኬቶች እድሳት ማድረግ | በቁጥር | 23 | 21 | 91 | |
| | በኢንዱስትሪዎች መካከል የምርትና ግብዓት ትስስር ኮንትራታዊ ውሎችን እንዲፈፀሙ ማድረግ፣ ግብዓቶቹ ለመፅደቃቸው ማረጋገጥ እና ደብዳቤ ማዘጋጀት | በቁጥር | 30 | 23 | 76.7 | |
| | የግብዓት መጠቀሚያ/ መሸጫ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄን ማስተናገድ | በቁጥር | 6 | 1 | 16.7 | |
| | አዲስ የሁለተኛ ታሪፍ ምድብ ሀ ማበረታቻ ተጠቃሚዎች ጥያቄ ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ግብዓት ምርት ጥመርታ በማዘጋጀት ሰርተፍኬት መስጠት | በቁጥር | 5 | 7 | 140 | |
| | የነባር ሁለተኛ ምድብ ሀ ታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚነት ጥያቄ ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና ግብዓት ምርት ጥመርታ በማዘጋጀት ሠርተፊኬት ማደስ | በቁጥር | 17 | 8 | 47 | |
| 7 | ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል ማሳደግ | | | | | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ግቦች | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት /የመጀመሪያ ሩብ ዓመት/ | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ | |
| | ጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑዘርፍ | በቁጥር | 1,426 | 926 | 65 | ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 264 ሴቶች ናቸው፡፡ |
| | ምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል | ›› | 18,269 | 6,578 | 36 | ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 1,598 ሴቶች ናቸው፡፡ |
| | ብረታብረትና ኤሌክትሮኒክስ | ›› | 900 | 666 | 74 | ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 222 ሴቶች ናቸው፡፡ |
| | ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች | ›› | 1664 | 1825 | 110 | |
| | አነስተኛ እና መካከለኛ | ›› | 19,669 | 9,464 | 48 | |
| | ድምር | በቁጥር | 41,928 | 19,459 | 46 | |
| 8 | የአረንጓዴ ማኑፋክቸሪንግ ስትራቴጂና ኢነርጂ ኢፊሽንሲ ስትራቴጂ በመተግበር የካርበን ልቀትን መቀነስ | | | | | |
| | የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት /MRV ስርአት መዘርጋት የሚያስችል መግባቢያ ሰነድ ማዘጋጀት | በቁጥር | 6 | 6 | 100 | ከስድስቱም ተጠሪ ተቋማት ጋር MRV ስርአት መዘርጋት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን ለመፈራረም በሂደት ላይ ነው፡፡ |
| | የችግኝ ተከላ ማካሄድ | በዙር | 3 | 3 | 100 | የአረንጓዴ አሻራ <<ኢትዮጵያን እናልብሳት>> በሚል መርሃ ግብር በ 3 ዙር 12000 የተለያዩ ችግኞች በቦሌ ለሚና በቅሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተከላ ተከናውኗል፡፡ |
| | የፋብሪካዎችን የኃይል አጠቃቀም መጠን እና አይነት ደረጃ (baseline) ጥናት ማካሄድ | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| **ሐ** | **የጥናትና ምርምር አቅምን ማጎልበት (ትኩረት መስክ ሦስት)** | | | | | |
| | የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 2 | -- | | ጥናቶች ተጀምሯል፤ |
| | የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 13 | -- | | የተጀመሩ ጥናቶች ብዛት 10፤ |
| | የምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 4 | 2 | 50 | |
| | የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | በቁጥር | 3 | 2 | 67 | |